QuickNotes mcps

ሪፖርት ካርዶች፡- የወላጅ መመርያ

ወላጆች፣ የልጃችሁ የመጀምርያ ሪፖርት ካርድ ወደ መኖርያ ቤት ኖቨምበር 13 ይመጣል። ሪፖርት ካርዶች በሚቀጥሉት እለቶችም ወደ ቤት ይላካሉ።

- ጃኗሪ 30
- ኤፕሪል 9
- ጁን 19 (ሪፖርት ካርዶች በፖስታ ቢት በኩል ይላካሉ)

በመካከለኛ ደርጃ እና/ወይም በ2ኛ ደረጃ ትም/ቤት ልጅ ካለዎት፣ ውጤቶችን በመስመር ላይ በድር የተመሰረተ መሳርያ፣ Edline ሊደርሱባቸው ይችላሉ።

በዚህ አመት፣ ሁሉም ከK–5 ክፍሎች የሚገኙ ተማሪዎች ልጅዎ በምን ሁኔታ እንዲያከናውንና እንደሚገሰግስ መረጃ ይበልጥ የሚሰጥ አዲስ ሚዛኖችን የጠበቀ ሪፖርት ካርድ ይቀበላሉ። MCPS የተማሪዎችን ግስጋሴ የሚመዝንበትና ዘገባ የሚያደርግበት ዘዴ ለውጧል ይህም ከስርአተ ትምህርት 2.0፣ የዲስትሪክቱ ስራአተ ትምህርት ጋር ለማቀናጀት የተደረገ ለውጥ ነው። ስለዚህ ይህ ለእርስዎና ለልጅዎ ምን ማለት ነው?

ዲስትሪክቱ አስተማሪዎች ስለሚመዝኑበት እና ስለልጅዎ ትምህርት ዘገባ ስለሚያደርጉበት ሶስት ቁልፍ ለውጦች አድርጓል።

- ✓ የመስረተ ትምህርት 2.0 መመዘኛዎች — ልጅዎ በያንዳንዱ የርእስ መስክ ማወቅ የሚያስፈልገውን እና መስራት መቻል ያለበት — አሁን Measurement Topics (መለኪያ ርእሶች)፣ ወይም የይዘትና የችሎታ መደቦች ናቸው።
- ✓ ሪፖርት ካርዶቹ በነዚያ መለኪያ ርእሶች ግስጋሴን ያንፀባርቃሉ። ይህም ማለት ልጅዎ በየርእሱ ስለሚያደርገው/ስለምታደርገው በይበልጥ የተዘረዘረ መረጃ ይቀበላሉ ማለት ነው።
- ✓ ውቴቶች አዳዲስ የውጤት አመልካቾች በመጠቀም ይዘገባሉ —ES (Exceptional - በጣም የላቀ)፣ P (Proficient - ብቁ) እና N (Not Yet Proficient - ገና ያልበቃ) ከ1ኛ እስከ 5 ክፍል

ተማሪዎች ሲሆን፣ ለሙአለህፃናት ተማሪዎች ደግሞ P (Proficient - ብቁ)፣ I (In Progress - በመገስገስ ላይ) እና N (Not Yet Proficient - ገና ያልበቃ)።

በዚያው ትም/ቤት በየክፍሉ ደረጃ ስለሚጠበቁ እና ተማሪዎች በያንዳንዱ ርእስ ስለሚማሩት ዝርዝሮች በአዲሱ አመት መጀመርያ ላይ በተላከላችሁ በስርአተ ትምህርት የወላጅ መመርያ ቀርበዋል።

ስለMCPS የውጤት አሰጣጥና ዘገባ አፈፃፀም ተጨማሪ መረጃ ፍላጎት ወይም ስለ በመመዘኛ-የተመሰረቱ ሪፖርት ካርዶች ጥያቄዎች አላችሁን? የውጤት አሰጣጥና ዘገባ አፈፃጸም ድር ጣብያ ጎብኙ።

## የበላይ ተቆጣጣሪ የደወል ሰአቶች እንዲለወጡ ሀሳብ አቀረቡ

የMCPS የበላይ ተቆጣጣሪ Joshua P. Starr (ጆሹዋ ፒ ስታር) የ2ኛ ደረጃ ትም/ቤት መጀመርያ ሰአቶች በ50 ደቂቃዎች ወደ ኋላ እንዲያሸገሽግ እና የኤሌሜንታሪ ትም/ቤቶች የትምህርት ቀን በ30 ደቂቃዎች እንዲራዘም ዲስትሪክቱ እንዲያገናዝብ ሀሳብ በማቅረብ ላይ ነው። ሃሳቡ የተመሰረተው፣ ባለፉት 10 ወራት የትም/ቤቶች መጀመርያና መጨረሻ ሰአቶች እና የተማሪ የመኝታ ልምዶች ተፅእኖ ሲያጠና በከረመው በ2013 Bell Times Work Group (የደወል ሰአቶች ግብራዊ ቡድን) ባቀረበው ዘገባ መሰረት ነው።

ዶ/ር ስታር የሚከተሉት ለውጦች እንዲጠኑ ያሳስባል፡-

- የ2ኛ ደረጃ ትም/ቤት መጀመርያ ሰአት በ50 ደቂቃዎች፣ ከ7:25 a.m. ወደ 8:15 a.m. ወደ ኋላ እንዲሸጋሸግ (የትምህርት መጨረሻ 3 p.m. እንዲሆን)።
 የመካከለኛ ደረጃ ትም/ቤት መጀመርያ ሰአት በ10 ደቂቃዎች፣ ከ7:55 a.m. ወደ 7:45 a.m. ወደ ፊት እንዲሸጋሸግ (የትምህርት መጨረሻ 2:30 p.m. እንዲሆን)።
- የኤሌሜንታሪ ትም/ቤት መጀመሪያ አሁን ባሉበት እንዲቆዩ (8:50 a.m.እና 9:15 a.m.)፣ የትምህርት ቀን ግን በ30 ደቂቃ እንዲራዘም (የትምህርት መጨረሻ 3:35 p.m. እና 4 p.m. እንዲሆን)።

በአሁኑ ወቅት፣ የኤሌሜንታሪ ትምህርት ቀን በMCPS 6 ሰአት ከ15 ደቂቃዎች ነው፣ ይህም ከመካከለኛና 2ኛ ደረጃ ትም/ቤት ተማሪዎች በ30 ደቂቃዎች ያጥራል። MCPS በሜሪላንድ ስቴት ውስጥ ሁለተኛ ያጠረ የኤሌሜንታሪ ትምህርት ቀን አለው።

በቀረበው ሀሳብ ላይ ከተማሪዎች፣ ሰራተኞች/መምህራን፣ ወላጆች እና ከማህበረሰብ ሰፊ ህዝባዊ አስተያየት ይፈለጋል። የድጋፍ ዘመቻ ጥሪው አራት ህዝባዊ ስብሰባዎች ያካትታል፣ የመጀምርያውም ሰኞ ኦክቶበር 28 ከ7p.m. – 8:30 p.m. Paint Branch 2ኛ ደረጃ ትም/ቤት ይሆናል። የደወል ጊዜዎች ዘመቻ የተለዩ ቡድኖች፣ መጠየቂያዎች፣ እና ሌሎች የማህበረሰብ አስተያየት የመስጠት እድሎችን በተጨማሪ ያካትታል። ቆየት ብሎ በዚህ ወር መጨርሻ ላይ ሙሉ መግለጫና የተሳትፎ ፕላን በማስታወቂያ መልክ ይነገራል። አስተያየቶችም በbelltimes@mcpsmd.org ኢሜይል ማድረግ ይቻላል።

ለተጨማሪ መረጃና የ2013 የስራ ቡድን ዘገባ ለማንበብ፣ የBell Times ድር ጣብያ ጎብኙ።

የበላይ ተቆጣጣሪ ስታርን ለ2013 አመታዊ ዘገባ ተቀላቀሉት።

ሰኞ ኖቨምበር 11፣ በስትራትሙር የሙዚቃ ማእከል የበላይ ተቆጣጣሪ ጆሹዋ ስታርን ሁለተኛ አመታዊ የትም/ቤቶች ይዘት ዲስኩር ለመስማት እንዲገኙለት ተጋብዘዋል። ዶ/ር ስታር ዲስትሪክቱ እንዴት ሁሉንም ተማሪዎች ለወደፊታቸው ስኬት ሊያዘጋጃቸው እንደሚችል ራእዩን ያጋራል። በአሉ ለህዝብ ነጻና ክፍት ነው። ከቀላል ቁርስና በስትራትሙር የሙዚቃ ማእከል በሞላ የMCPS ተማሪዎች ትርእይቶችና ስነጥበባት አቅርቦቶች በ7:30 a.m. ይጀምራል። በ8:30 a.m፣ ዶ/ር ስታር የትም/ቤቶች ይዘት ዲስኩሩን ያቀርባል። ድርጊቱ በ9:30 a.m. እንደሚያልቅ ይጠበቃል። የውጭ ቋንቋ ትርጉምና የምልክት ቋንቋ ይኖራል።

ኖቨምበር 11 ሊገኙልን ፕላን ካለዎት ያስታውቁን። እስከ ኖቨምበር 1 ድረስ በwww.mcpsstateoftheschools.org እባክዎን ያስታውቁን።

በMCPS የውጭ አካባቢ ትምህርት የ50 አመት በአል!

የMCPS የውጭ አካባቢያዊ ትምህርት ፕሮግራም የ50ኛውን አመት የማስተማርና የመማር ፕሮግራም ምክንያት በማድረግ የውጭ አካባቢ ትምህርት በአል ኦክቶበር 26 ያከብራል! ክውነቱ በLathrop E. Smith Environmental Education Center, 5110 Meadowside Lane, Derwood ከ10:00 a.m. – 1:00 p.m. ይካሄዳል።

Outdoor Ed Program (ከቤት ውጭ የትምህርት ፕሮግራም) በአመት ውስጥ ለ25,000 ተማሪዎች ያገለግላል። የእውቀት ይዘት ይገነባል፣ አእምሮን በፈጠራዊ ፕሮብሌም አፈታት የሚያውሉ ተመክሮዎች ያቀርባል፣ እናም በትብብር አብሮ የመስራት ችሎታን ያጠናክራል።

ኑና የደጅ አከባቢያዊ ትምህርት ምን እንደሆነ ተመልከቱ! ክውነቱ የመማርያ ጣብያዎችን፣ በሆዳቸው የሚሳቡና የጥንት አራዊቶች፣ የአካባቢያዊ ግጥሚያዎችና ሌላም-ሌላም ያቀርባል። ከMagruder 2ኛ ደረጃ ትም/ቤት ነፃ መጓጓዣ አገልግሎት ይቀርባል።

ለተጨማሪ መረጃ፣ እባክዎን 301-924-3123 ይደውሉ።

ወደ Montgomery አለም በአል ይምጡ

የMontgomery አለም በአል የMontgomery County እና የመላ ዋሺንግቶን ዲሲ አካባቢ የበለፀገ ባህላዊ ቅርሶችን ያከብራል ያሳያልም። በአሉ የሚዘጋጀው በWestfield Wheaton Plaza Mall መኪና ማቆሚያ ሜዳ (ሜትሮ ጣብያ አጠገብ) እሁድ ኦክቶበር 20 2013 ከእኩለቀን እስከ 5:00pm ነው።

በFund for Montgomery ስፖንሶር የተደረገና በKID Museum የተደራጀው ነፃ በአል አለም-አቀፍ መንደር፣ የባህላዊ ምግቦች አቅርቦት፣ የእጅ ስራ ገበያ፣ የተለያዩ ባህሎች ሰልፍ፣ ሁለት የባህላዊ

ጭፈራና ሙዚቃ መድረኮች፣ በአገልግሎት ግንኙነቶች፣ ባህላዊ ስነጥበባት እና ለመላ ቤተሰብ የሚሆን የደስታ ግንኙነቶችን ያካትታል።

ለተጨማሪ መረጃ፣ www.worldofmontgomery.com ይጎብኙ።

## በMontgomery County አመታዊ የማህበረሰብ አገልግሎት ሳምንት ይሳተፉ!

የMontgomery County አመታዊ የማህበረሰብ አገልግሎት ሳምንት ለተማሪዎች የStudent Service Learning (የተማሪዎች የአገልግሎት ትምህርት) (SSL) ሰአቶች ለማግኘት፣ እናም ከቤተሰብ ወይም ከጓደኞች ጋር በጠቃሚ እንቅስቃሴ ለመሳተፍ አይነተኛ እድል ነው። የማህበረሰብ አገልግሎት ሳምንት በኦክቶበር ከ20 እስከ 27 ነው። ለተጨማሪ ዝርዝሮች የMontgomery County Volunteer Center ድር ጣብያ ጎብኙ።

## Trades Foundation የመኪና ስጦታዎች ይፈልጋል

የMontgomery County Students Automotive Trades Foundation (የተማሪዎች የመኪና ጥገና ድርጅት) (ATF) የመኪና ስጦታዎች እየፈለገ ነው። ስጦታዎ 350 የሚደርሱ የ2ኛ ደረጃ ትም/ቤት ተማሪዎችን መኪናዎችን መመርመር፣ መጠገና ማደስ ለመማር ሊያግዛቸው ይችላል። ATF ተማሪዎችን የእንክብካቤ፣ የጥገና፣ የሽያጭና የግብይት ተግባራዊ ስልጠና በመስጠት የመኪና ምህንድስና (automotive) ትምህርት የሚሰጥ በጎ አድራጎት ነው። መኪኖችን የautomotive ፕሮግራም ባላቸው በDamascus፣ Gaithersburg፣ Seneca Valley ወይም Thomas Edison የ2ኛ ደረጃ ትም/ቤቶች መስጠት ይቻላል። ሰጭዎች የታክስ ቅናሽ የማግኘት ብቃት አላቸው።

ለተጨማሪ መረጃ፣ የATF ድር ጣብያ ይጎብኙ እና Donate Your Car የሚለውን ትር ጠቅ አድርጉ። ወይም፣ Mike Snyder (ማይክ ስናይደር)ን በ301-929-2164 ተገናኙ።